የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 60
ADDIS ABABA July 10th, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፮/፪ሺ፲፪

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ................................................ገጽ ፲፪ሺ፮፻፲፱

**Content**

Proclamation No. 1206/2020

Public Enterprises Privatization Proclamation Page……………………………………………...12619

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፮/፪ሺ፲፪

## የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ እና ለግል ኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ የፖሊሲ ከባቢዎችን ለመፍጠር የሕግ ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ አፈጻጸም አስተዋጽዎ እንዲኖረው ለማድረግ ለልማት የሚውልን የፋይናስ አቅርቦት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## PROCLAMATION NO. 1206 /2020

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PRIVATIZATION OF PUBLIC ENTERPRISES

**WHEREAS,** it has become necessary to introduce reforms to sustain the country’s economic growth and transformation and to create an enabling policy environment for private sector investment;

**WHEREAS**, it has become necessary to improve the provision of finance for development to contribute to implementation of the country’s economic growth strategy;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://ethiodata.et/

የግል ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ሚናና ተሳትፎ ማስፋፋትና ማዳበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ቅልጥፍና ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ ለካፒታል ያላቸውን ተደራሽነት እና የአገልግሎታቸውን ጥራትና ተደራሽነት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሰፊ መሠረት ላይ የተጣለ ይፋና ግልጽ የሆነ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፮/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "**ፕራይቬታይዜሽን**" ማለት የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ለግል ዘርፉ በሽያጭ የማስተላፍ ውጤት የሚያስከትል ግብይት ነው፤

**WHEREAS**, it has become necessary to broaden the role and participation of the private sector in the economy;

**WHEREAS**, it has become necessary to improve the efficiency of public enterprises, enhance their competitiveness, improve their access to capital and improve the quality and accessibility of their services;

**WHEREAS**, to achieve this objective it is found necessary to implement of a privatization program in an open and transparent manner;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Public Enterprises Privatization Proclamation No. 1206/2020".

2. **Definition**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "**Privatization**" means a transaction or transactions resulting in either a sale of assets or share capital of a Public Enterprise, in full or in part, to private ownership;

https://ethiodata.et/

፪/ **"የመንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ የሚተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

፫/ **"ቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች"** ማለት በሚኒስቴሩ የሚከናወን የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል ለማዛወር የታቀደ ማናቸውም ዝግጅት ወይም ሂደት ነው፤

፬/ **"ወርቃማ አክሲዮን"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅትን በመለወጥ የካፒታሉ አካል የሆነና በማናቸውም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቶችን ለመንግሥት የሚያጎናጽፍ በአክሲዮን መመስረቻ ፅሁፍ ውስጥ የተደነገጉ ልዩ መብቶችን የያዘ አክሲዮን ነው፤

፭/ **"ኤጀንሲ"** ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤

፮/ **"ሚኒስቴር"** እና **"ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደምተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፯/ **"ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን"** ማለት ኤጀንሲውን ጨምሮ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት የመንግሥት የባለቤትነት መብቶችን ለመከታተል፣ ለመጠበቅ፣ ለመተግበር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰየመ ባለሥልጣን ነው፤



2/ "**Public Enterprise**" means an Enterprise governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992;

3/ "**Pre-Privatization Activities**" means any activity or process performed by the Ministry intended to prepare a Public Enterprise for privatization;

4/ "**Golden Share**" means a share in the capital of a company, formed by conversion of a Public Enterprise pursuant to this Proclamation, carrying such special rights as are set out in the Articles of association of the company to enable the Government to protect the national interest with voting and veto rights over any board resolution;

5/ "**Agency**" means the Public Enterprise Holding and Administration Agency;

6/ "**Ministry**" **or** "**Minister**" means the Ministry of Finance or the Minister of Finance, respectively;

7/ "**Supervising Authority**" means an authority, including the Agency, designated by the Council of Ministers with a view to monitoring, protecting and exercising the ownership rights of the Government in accordance with Public Enterprise Proclamation No. 25/1992;

፰/ “ባለአደራ” ማለት በሚኒስቴሩ ሥር የተደራጀ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ዳይሬክቶሬት ጄነራል ነው፡፡

፱/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>የፕራይቬታይዜሽን ዓላማዎች</u>

የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚደግፍ በግልፅነት፣ በአሳታፊነትና በተአማኒነት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ሲሆን የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማነትን ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ የቴክኒክ ሙያንና ክህሎትን መጋበዝ እና የካፒታል አቅርቦትን ማሻሻል፤

፪/ መንግሥት የሚያካሂዳቸውን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ለማጎልበት ገቢዎችን ማሰባሰብና የልማት ፋይናንስ አቅርቦትን ማጎልበት፤

፫/ ለግል ኢንቨስትመንት የፖሊሲ ከባቢዎችን በማጎልበትና የግል ዘርፉን መስፋፋት በማበረታታት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማሳደግ፡፡

8/ "**Trustee**" means the Trustee Directorate General organized within the Ministry.

9/ "**Person**" means a natural person or a juridical person;

10/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Objectives of Privatization</u>

The privatization program shall support the country’s economic growth and transformation, be conducted based on the principles of transparency, openness and integrity, and shall have the following objectives:

1/ To improve the efficiency of Public Enterprises, enhance their competitiveness, attract technical expertise and skill sets, and improve access to capital;

2/ To generate revenue and enhance the provision of development finance in order to promote financing activities undertaken by the Government;

3/ To promote the Country's economic development by enhancing the policy environment for private investment and encouraging the expansion of the private sector.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ሁለት

## ስለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች

**፬. ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች የተለያዩ አካላት ኃላፊነት**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚኒስቴሩን እና የተቆጣጣሪውን ባለሥልጣን የውሳኔ ሃሣብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል መዞር ያለበትን የልማት ድርጅት ይወሰናል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) ማናቸውንም የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች የሚያከናውን ሲሆን የሚመለከተውን የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በማማከር የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደት መቼ መጀመር እንዳለበትና የትኞቹ ሥራዎችም መካተት እንዳለባቸው፣

ለ) ከመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመመካከር የእያንዳንዱን ሽያጭ አመላካች የሽያጭ ዋጋ (ወይም መነሻና መድረሻ ዋጋ) እና ወደ ግል የሚዛወረውን የአክሲዮን መጠንን (የድርጅቱን መጠን)፣

ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ዋጋ ግምትን፣ እንደገና የማዋቀር ጥረቶች ውጤቶችን፣ ወቅታዊው የገበያ ሁኔታዎችን እና ድርጅቱ ኢንቬስተሮችን መሳብ የመቻሉን ዕድል ከግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ለመዛወር ያለውን ዝግጁነት፣ ይወስናል፡፡

## PART TWO

## PRE-PRIVATIZATION ACTIVITIES

**4.Responsibilities of Different Institutions for Pre-Privatization Activities**

1/ The Council of Ministers shall determine the Public Enterprise to be fully or partially privatized, taking into consideration the recommendations of the Ministry and the Supervising Authority of the Public Enterprise.

2/ The Ministry : -

a/ Shall determine any necessary Pre-privatization activities including when to begin the Pre-privatization process and which activities shall be included in coordination with the Supervising Authority of the Public Enterprise;

b/ In consultation with the Supervising Authority of the Public Enterprise, shall determine the modality of each sale along with an indicative price (or price range) and number of shares (or proportion of the company) to be privatized;

c/ Shall determine the readiness of each Public Enterprise for privatization, taking into account factors including but not limited to the Public Enterprise's valuation, results of any restructuring efforts, current market conditions and the likelihood that the Public Enterprise will attract investors.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ መሆኑ ታምኖ የፕራይቬታይዜሽን ስልቱ ሲወሰን ኤጀንሲው ፕራይቬታይዜሽኑን የመተግበር እንቅስቃሴ ይጀምራል፡፡

፬/ ወደ ግል የሚዛወር የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፦

ሀ) ከሚኒስቴሩ እና ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቱን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይሰጣል፤

ለ) ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመመካከር በሚኒስቴሩ በተሰጡ መመሪያዎች መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽንና ለፕራይቬታይዜሽን ያዘጋጃል፤

ሐ) በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደትና በፕራይቬታይዜሽን ወቅት የልማት ለብክነት አለመዳረጉን ያረጋግጣል፤

መ) በመደበኛው የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት ወይም በሚኒስቴሩ ስምምነት ካልሆነ በቀር፣ በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ወቅትና በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ማናቸውም አዲስ ኢንቬስትመንት ከማድረግ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

3/ Once a Public Enterprise is deemed ready for privatization and the privatization modality has been determined, upon the recommendation of Ministry, the Agency shall commence implementation of the privatization transaction.

4/ The Management Board of a Public Enterprise to be privatized shall:

a) Provide the Ministry and the Supervising Authority all information regarding the Public Enterprise as requested;

b) Prepare the enterprise for pre-privatization and privatization in accordance with instructions given to it by the Ministry, in consultation with the Supervising Authority;

c) Ensure that the assets of the Public Enterprise do not deteriorate or become dissipated during the pre-privatization or privatization phases;

d) Refrain from making any new investments during the privatization or pre-privatization phases except in the ordinary course of business or with the agreement of the Ministry.

https://ethiodata.et/

**፭. <u>በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንደገና ስለማዋቀርና ሌሎች ተግባሮች</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት የልማት ድርጅቱ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት ተገቢው የካፒታል አደረጃጀቶች፣ የንግድ ስትራቴጂ፣ የኮርፖሬት አስተዳደር መዋቅሮች እና የሪፖርት አቀራረብና የመረጃ አገላለጽ ልምዶች ያለው መሆኑን ይገመግማል፤ ጉድለት በሚኖርበትም ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

፪/ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚኒስቴሩን የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን እንቅስቃሴን ለመደገፍ በመንግሥት የልማት ድርጅቱ ላይ ክትትል ባደረገበት ወቅት ያደረጋቸውን ማናቸውንም የኦፐሬሽን ግምገማዎችንና ተዛማጅ መረጃዎችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም የኦፐሬሽንና የፋይናንስ ሥርዓትን እንደገና የማዋቀር ኃላፊነት አለበት፤ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊትም እንደገና መዋቀሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ዋጋና ተፈላጊነቱን የሚያሳድግ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ ከፕራይቬታይዜሽን በኋላ ተገቢ ያልሆነ የውድድር ባህርያት፣ የገበያ ልምዶች እና መጠኑ ያለፈ የገበያ የበላይነት እንዳይከሰት በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ወይም ወቅት በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፡፡

**5. <u>Public Enterprise Restructuring and Other Activities Prior to Privatization</u>**

1/ Pursuant to Article 4 (2) and (3) of this Proclamation, the Ministry, in coordination with the Supervising Authority, shall evaluate whether the Public Enterprise has the appropriate capital structure, business strategy, corporate governance structures and reporting and disclosure practices prior to privatization, and take appropriate action in the event of deficiencies.

2/ The Supervising Authority shall provide to the Ministry any financial and operational analyses, and related supporting information it has already conducted in the course of its oversight efforts to support the Ministry's pre-privatization activities.

3/ The Ministry shall be responsible for any operational or financial restructuring required and shall ensure that such restructuring is limited to bolstering the value of the Public Enterprise and attractiveness prior to privatization.

4/ The Ministry shall take all necessary action during the pre-privatization phase to prevent anti-competitive behavior, unfair market practices and excessive market dominance following privatization, in accordance with prevailing laws of the country.

https://ethiodata.et/

## ፮. <u>የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ስለመለወጥ</u>

፩/ የንግድ ሕግ አንቀጽ ፫፻፯ (፩) ቢኖርም፣ አንድን የመንግሥት የልማት ድርጅትን ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ ለማድረግ በአንድ ባለአክሲዮን ባለቤትነት ወደሚያዝ የአክሲዮን ማኅበርነት ሊለወጥ ይችላል፡፡

፪/ የልማት ድርጅቱ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት በሚለወጥበት ወቅት አክሲዮኖቹ ወደ ግል ባለቤትነት እስከሚዛወሩ ድረስ የድርጅቱ ካፒታል በአክሲዮኖች ተከፋፍሎ አክሲዮኖቹ በመንግሥት ይያዛሉ፡፡

፫/ በንግድ ሕጉ ለባለአክሲዮኖች ጉባዔ የተሰጡ ሥልጣኖች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ መሠረት አግባብነት ላለው የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንደተሰጡ ይቆጠራሉ፡፡

፬/ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ ፫፻፯ (፩) ፣ አንቀጽ ፫፻፲፩፣ አንቀጽ ፫፻፵፯ (፩) እና አንቀጽ ፫፻፵፱ በስተቀር ሌሎቹ የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፭/ በንግድ ሕጉ አንቀጽ ፭፻፵፮ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ አንቀጽ ፷፱ (፩) እና (፪) የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ሚኒስቴሩ የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክስዮን ማኅበርነት በሚለውጥበት ጊዜ ለአክሲዮን ማኅበሩ የሚተላለፉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቱን



## 6. <u>Conversion of a Public Enterprise to a Share Company</u>

1/ Notwithstanding Article 307 (1) of the Commercial Code, a Public Enterprise may be converted into a share company with only one shareholder in preparation for privatization.

2/ In the event the Public Enterprise is converted into a share company, the capital of the share company shall be divided in to shares which shall be held as government shares until such time as any shares are transferred to private ownership.

3/ Authorities given to shareholders meetings under the Commercial Code shall be deemed given to the Supervising Authority of the Public Enterprise in accordance with Public Enterprise Proclamation;

4/ All provisions of the Commercial Code shall be applicable, with the exception of the provisions of Articles 307(1), 311, 347(1) and 349.

5/ Notwithstanding Article 546 Sub-Articles (1) - (4) of the Commercial Code and Article 69(1) and (2) of the Income Tax Proclamation No. 979/2008, the Ministry shall, in converting a Public Enterprise into a share company, have the power to determine the assets and liabilities of the

https://ethiodata.et/

ሀብትና ዕዳዎች እንዲሁም ንብረቶቹ እንደገና ከተገመቱ በኋላ ካፒታሉን የመወሰንና የማሳደግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፮/ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደተመዘገበ ህልውናው ያከትማል፡፡

## ፯. የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ዋጋ ስለመተመን

፩/ ሚኒስቴሩ የልማት ድርጅትን፣ የልማት ድርጅትን የተወሰነ ክፍል ወይም ንብረት ወይም የመንግሥት አክሲዮንን ወደ ግል ለማዛወር በቅድሚያ ዋጋው ገለልተኛ በሆነ ብቃት ባለው ባለሙያ እንዲተመን ማስደረግ አለበት፡፡

፪/ የዋጋ ትመናው የሚከናወነው በሚኒስቴሩ ቁጥጥር ሥር የሚደረገው የልማት ድርጅቱን የፋይናንስ እና/ወይም የኦፕሬሽን እንደገና የማደራጀት ሥራ መጠናቀቅ ተከትሎ ሚኒስቴሩ ባወጣው የዋጋ ትመና መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

፫/ በዋጋ ትመናው መሰረት የሚወሰነው የመሸጫ መነሻ ወይም አመልካች ዋጋ በፕራይቬታይዜሽኑ ሂደት በኤጀንሲው ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በሚኒስቴሩ መጽደቅ አለበት፡፡

Public Enterprise that may be transferred to share company, fix its capital and increase its capital after reevaluating its assets.

6/ A Public Enterprise converted into a share company shall cease to exist upon registration of the share company.

## 7. Valuation of Public Enterprise

1/ The Ministry shall cause an independent valuation of the Public Enterprise, its assets, units or government-owned shares by a qualified expert.

2/ The valuation shall be carried out following the completion of any financial and/or operational restructuring overseen by the Ministry and shall be conducted in accordance with guidelines issued by the Ministry.

3/ The floor or indicative price determined as the result of the valuation shall be subject to approval by the Ministry prior to its usage by the Agency in privatization process.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ሦስት

## የፕራይቬታይዚሽን አፈጻጸም ማዕቀፍ

### ፰. የፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸም

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸምን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከኤጀንሲው ውጭ ላለ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተጠሪ የሆነን የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተያዙ አክሲዮኖች ወደ ግል ማዛወሩ ከመከናወኑ በፊት ለኤጀንሲው መተላለፋቸውን ያፀድቃል፤

ለ) የሚኒስቴሩንና የኤጀንሲውን የውሳኔ ሀሳብ ከግምት ውስጥ በማስገባት የማናቸውም ወርቃማ አክሲዮን አጠቃቀም፣መዋቅር እና አተገባበሩን ያፀድቃል፤

፪/ ኤጀንሲው የፕራይቬታይዜሽንን አፈጻጸም በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) የሽያጭ ማከናወኛ ሥነ ሥርዓቶችን ያዘጋጃል፤

ለ) ለእያንዳንዱ ሽያጭ የሚያገለግል የጨረታ መመዘኛ መስፈርቶችን ይወስናል፤

ሐ) የመሸጫ ጊዜን ይወስናል፣እያንዳንዱን ሽያጭ ያመቻቻል፣ ሽያጩን በበላይነት ይከታተላል፤

መ) ሽያጭ ሲከናወን የሚያግዙ ባለሙያዎችን ይቀጥራል፤

## PART THREE

## PRIVATIZATION IMPLEMENTATION FRAMEWORK

### 8. Privatization Implementation

1/ The Council of Ministers shall have the following Powers and Duties with respect to privatization implementation activities:

a) For a Public Enterprise accountable to a Supervising Authority other than the Agency , approve the transfer of the Public Enterprise to the Agency prior to the privatization transaction;

b) Approve the use and structure of any golden share, and the exercise thereof, taking into account the recommendation of the Ministry and the Agency.

2/ The Agency shall have all the functions necessary for the implementation of privatization and shall in particular include the following:

a) Develop procedures for conducting sales;

b) Determine the bid evaluation criteria for each tender transaction;

c) Determine the timing of sale, organize and oversee each transaction;

d) Hire experts as needed to assist in carrying out transactions;

https://ethiodata.et/

ሠ) ፍላጎት ያላቸው ኢንቬስተሮች በግብይቱ እንዲሳተፉ ከበቂ ጊዜ ጋር ሽያጩን በሕዝብ መገናኛ ያሳውቃል፤

ረ) አስፈላጊውን ሰነዶችና ናሙና ውሎችን ያዘጋጃል፤

ሰ) በማናቸውም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት መስፈርቶች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሸ) ማንኛውም ባለሀብት በረዥም ጊዜ በሚፈጸም ክፍያ የሽያጩን ዋጋ የመክፈል መብት የሚሰጠው መሆን አለመሆኑን እና ክፍያ የሚፈጸምበትን ሕጋዊ ገንዘብ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመመካከር ይወስናል፤

ቀ) የፕራይቬታይዜሽን ሂደት አተገባበሩ ሥርዓት ያለው፣ ሕጋዊ፣ግልጽና ቀልጣፋ መሆኑን ያረጋግጣል፤

በ) ከፕሮግራሙ አፈጻጸም ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ለመንግሥት የውሳኔ ሃሣብ ያቀርባል፤

ተ) ከሕዝብ ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም እንቅስቃሴዎችን ወይም ክንዋኔዎችን ያስተዋውቃል፡፡

፫/ የመንግሥት የልማት ድርጅት ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ መሆኑ ከተረጋገጠ እና የፕራይቬታይዜሽን ስልቱ በሚኒስቴሩ ሲወሰን ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፬) በተደነገገው መሠረት ለዚሁ ባቋቋመው ክፍል አማካይነት ወደ ግል የማዛወሩን ተግባር ማከናወን ይጀምራል፡፡

e) Publicize the offering appropriately providing sufficient time for interested investors to participate in the transaction;

f) Prepare all necessary documentation and sample agreements;

g) Decide on any post-privatization investment requirements;

h) In consultation with the Ministry, decide whether to grant the right to any investor to pay for sales on an installment basis and the currency of payment;

i) Ensure the systematic execution, legality, transparency and efficiency of the privatization process;

j) Submit recommendations to the Government as may be appropriate on policy issues relating to the implementation of the program; and

k) Communicate with the public and publicize the activities of the privatization program.

3/ Pursuant to Article 4 sub-Article (2)-(4) of this Proclamation, once a Public Enterprise is deemed ready for privatization, and the privatization modality has been determined by the Ministry, the Agency shall commence the implementation of the privatization transaction, through a dedicated unit at the Agency.

https://ethiodata.et/

፬/ ኤጀንሲው ከሚኒስቴሩ ጋር በመቀናጀት የመሸጪያ መነሻ ዋጋ ወይም በግብይት ወይም በንግድ ላይ የተመሠረተ ተመሳሳይ ዋጋ ወይም በውድድር ላይ የተመሠረተ ጨረታ ወይም በጨረታ ላይ የተመሠረተ ተመሳሳይ ሽያጭ ከመጀመሩ ቀድም ብሎ የሚቀርበውን የመጨረሻውን የሽያጭ መጠንን እና የአክሲዮን ዋጋን ይወስናል፡፡

፭/ ኤጀንሲው ፕራይቬታይዜሽንን፣ ለሽያጭ የሚቀርበውን የአክሲዮን ዋጋን ወይም መጠንን ወይም የልማት ድርጅቱን ድርሻ በተመለከተ የቀረበውን ሀሳብ በገበያው፣ በዘርፉ ሁኔታዎች ወይም በሌሎች ምክንያቶች መቀያየር ማሻሻል የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ ለሚኒስቴሩ መልሶ ያሳውቃል ፡፡

፮/ የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ ግል ማዛወር ያልተቻለ እንደሆነ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን አግባብ ባላቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሕግ መሠረት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥያቄ አቅርቦ ሲፀድቅለት የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ሊፈርስ ይችላል፡፡

4/ The Agency shall determine, in collaboration with the Ministry the final offering size and share price immediately before the commencement of an Initial Public Offerings (“IPO”) or similar exchange- or trading-based share offering or based on final transaction negotiations in the case of competitive bid or similar tender-based sale.

5/ The Agency shall revert to the Ministry for their agreement in the event the recommended modality for privatization or the recommended share price or number of shares (or proportion of company) to be offered requires modification as a result of changing market or sector conditions or other factors.

6/ Where a Public Enterprise privatization transaction fails, upon request by the Supervising Authority to the Council of Ministers and approval thereof and in accordance with relevant provisions of the Public Enterprises law, the Public Enterprise may be dissolved.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አራት

## የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች

### ፱. የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች

፩/ በሥራ ላይ የሚውል ማናቸውም የፕራይቬታይዜሽን ስልት አተገባበር በግልጽነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ እና ግቡም ለመንግሥት ተስማሚ የሆኑ ስምምነቶች ላይ መድረስ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከዚህ በታች ከተመለከቱት የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች አንዱ እንደአግባቡ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፤

ሀ) በውድድር ላይ በተመሠረተ ጨረታ፤

ለ) ለሕዝብ ክፍት በሆነ ጨረታ፤

ሐ) የአክሲዮን ገበያ ወይም ሌሎች ተስማሚ የግብይት መድረኮች ያሉ እንደሆነ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ለሽያጭ በሚቀርብ አክሲዮን፤

መ) በረዥም ጊዜ ተከፋፍሎ በሚሸጥ የተሰበጣጠረ ግገር፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በሚኒስቴሩ ፈቃድ ተስማሚና ለኢንዱስትሪው ደረጃ የሚመጥን የንግድ ወይም የስትራቴጂክ ሽያጭን በቅድሚያ በተመረጡ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው የኮርፖሬት ኢንቬስተሮች ላይ ያነጣጠረ ሽያጮችን የመሳሰሉ ሌሎች የፕራይቬታይዜሽን ስልቶችን መምረጥ ይችላል፡፡ጠቀሜታቸው በበቂ ምክንያት የተደገፈ ከሆነ ሂደቱም በተቻለ መጠን በግልጽነት መሆን ይኖርበታል፡፡

## PART FOUR

## MODALITIES OF PRIVATIZATION

### 9. Modalities of Privatization

1/ The use of any transaction modality of privatization shall be based on the principles of transparency and the goal of securing the most favorable terms for the Government.

2/ In accordance with Sub-article (1) of this Article, any one of the following modes of privatization may be used as appropriate:

a) Competitive tender;

b) Public auction;

c) Initial Public Offerings (“IPO”); where there is a stock exchange or other suitable trading platform and

d) Sales, featuring sale tranches over time.

3/ Notwithstanding Sub Articles (1) of this Article the Agency may after approval from the Ministry, select other privatization modalities that are appropriate and are industry standard, such as trade or strategic sales (targeted to a small number of pre-selected corporate investors),If they are the most appropriate for the circumstance, provided there is a clear justification for their use and the process is carried out in as transparent manner as possible.

https://ethiodata.et/

፬/ የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም፣ ሚኒስቴሩ ከኤጀንሲው ጋር በመመካከር ከሚሸጡት አክሲዮኖች ውስጥ የተወሰኑት በመንግሥት የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ተለይተው የሚያዙበትን ሁኔታ እና የአክሲዮኖቹን ዋጋና መጠን ይወስናል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፕራይቬታይዜሽን ሽያጭ የመንግሥትን አክሲዮኖች መቶ በመቶ ወይም ከፊሉን ሊያካትት ይችላል፡፡

፮/ አብላጫውን ወይም ወሳኝ የሆኑ አክሲዮኖችን ሽያጭ በሚመለከት መንግሥት ወርቃማውን አክሲዮን ማስቀረትን መምረጥ ይችላል፡፡ ወርቃማ አክሲዮን መንግሥት የሕዝብ ጥቅምን አያስጠብቅም ብሎ ባመነበትን በማናቸውንም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምጽ የመሻር መብት ያጎናጽፈዋል፡፡

፯/ የፍታብሔር ሕግ አንቀጽ ፩ሺ፯፻፶ ድንጋጌ ቢኖርም፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የሽያጭ ዋጋ የሚከፈለው በውሉ በተመለከተው ሕጋዊ ገንዘብ ይሆናል፡፡

4/ Notwithstanding the privatization modality, the Ministry, in consultation with the Agency, shall decide if a portion of a Public Enterprise shares shall be reserved for sale to the Public Enterprise employees including the amount of the share reserved for employees and the price of each share,

5/ Pursuant to Article 4 sub-Article (1) of this Proclamation, privatization sales may include hundered percent of the Government's shares or any portion of shares thereof.

6/ The Government may choose, in the case of the sale of a majority or controlling interest, to retain a golden share. A golden share shall provide the Government with voting and veto rights over any board resolution which it believes is not in the public's interest.

7/ Notwithstanding the provision of Article 1750 of the civil code, the price of the enterprise shall be paid in the currency specified in the contract.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አምስት

## ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ታሳቢዎችና ግምገማዎች

**፲. ድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ታሳቢዎች እና ግምገማዎች**

፩/ የድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ግዴታዎች የፕራይቬታይዜሽን ውሉ አካል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

፪/ የልማት ድርጅት ገዢ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በሽያጭ ውሉ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ማናቸውንም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ኤጀንሲው የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ግዴታዎች አፈጻጸምን ይከታተላል፡፡

፬/ ባለሀብቱ የውል ግዴታዎችን ለመከታተል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለኤጀንሲው በየጊዜው የማቅረብ እና የኤጀንሲው ተወካዮች ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በማናቸውም ጊዜ ወደ ተሸጠው የልማት ድርጅት እንዲገቡና ግምገማ እንዲያካሂዱ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡

**፲፩. ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ግምገማ**

፩/ ኤጀንሲው በፕራይቬታይዜሽን ክንውኑ ላይ ግምገማ የሚያካሂድ ገለልተኛ ባለሙያ በመሾም በግኝቶቹ ላይ ዓመታዊ ሪፖርት ማውጣት ይኖርበታል፡፡

## PART FIVE

## POST PRIVATIZATION CONSIDERATIONS AND EVALUATION

**10. Post Privatization Investment Considerations**

1/ Post-privatization investment obligations maybe included in a privatization agreement when warranted.

2/ A purchaser of a Public Enterprise shall be obliged to implement, within the time limit specified and as agreed in the sales contract, any post-privatization investment.

3/ The Agency shall monitor the execution of any post-privatization obligations.

4/ The investor shall be obliged to periodically submit to the Agency information that is necessary for monitoring contractual requirements and to allow the representatives of the Agency to enter and inspect the enterprise at any pre-arranged time to make assessments.

**11. Post Privatization Evaluation**

1/ The Agency shall commission an independent expert to conduct an evaluation of the privatization transactions undertaken and issue an annual report of its findings.

https://ethiodata.et/

፪/ የግምገማው ሪፖርት የተላለፉና ቀሪ የሆኑ ወይም የተከፈሉ የመንግሥት ዕዳዎችን፣ የመንግሥት ዋስትናዎች ያሉበትን ደረጃና ሌሎች ተያያዥ ዕዳዎችን፣ ወደ ግል በተዛወረው የመንግሥት የልማት ድርጅት የመንግሥት ገንዘብ ያለመኖር ያስከተለውን ተፅዕኖ ወይም ውጤቶች፣ በግል ዘርፉ ውጤታማነት መገምገም ይኖርበታል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የግምገማ መለኪያዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

**፲፪. ስለ ልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታ መተላለፍ**

፩/ ወደ ግል የተዛወረ የመንግሥት የልማት ድርጅት በአክሲዮን ማኅበርነት እንደተመዘገበ ህልውናውን ያጣል፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ መብቶችና ግዴታዎች በሽያጭ ውሉ መሠረት ለገዢው መተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች ወደ ገዢው እንደማይተላለፉ በሽያጭ ውሉ ውስጥ ስምምነት ከተደረገ ከዚሁ ጋር የተያያዙ መብትና ግዴታዎች ወደ ባለአደራ ይተላለፋሉ፡፡

2/ The evaluation report shall assess transfer or extinguishment of government liabilities, status of any government guarantees and other contingent liabilities, effects of the absence of government funding on privatized Public Enterprises, assessment of efficiency gains realized by the private sector, and shall include other assessment measurement parameters as necessary.

**12. Transfer of Rights and Obligations of Public Enterprises**

1/ A privatized Public Enterprise shall cease to exist upon the completion of registration of the share company. The rights and obligation of the Public Enterprise shall be transferred to the buyer pursuant to the sales contract.

2/ Notwithstanding the Provisions of Sub-Article (1) of this Article, rights and obligations pertaining to receivables and payables shall be transferred to the trustee where the sales contract provides for the non-transferability of such receivables and payables to the buyer.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ከሚኒስቴሩ ውሳኔ በኋላ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ወደ ተለወጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ከተላለፉት ሀብትና ዕዳዎች ላይ ዕዳቸው ተከፍሎ የቀሩ ንብረትና ዕዳዎች ወደ ባለአደራ መተላፍ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፹፯ መሠረት በኤጀንሲው በተሰጠ ውሳኔ ለቀድሞው ባለንብረቶች ለተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚተላለፉ መብትና ግዴታዎችን በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፭/ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት የነበረ የጡረታ ሽፋን ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡ የአዲሱ ድርጅት ባለቤት የሠራኞችን ጡረታ በተመለከተ አግባብ ባላቸው ሕጎች በአሠሪዎች ላይ የተጣሉትን ግዴታዎች ማክበር ይኖርበታል፡፡

## ፲፫. <u>አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

፩/ በውላቸው ውስጥ በግልጽ በተመለከተ የግልግል ዳኝነት ሂደት ወይም አካል እንዲታይ የተስማሙ ካልሆነ በስተቀር፣ በኤጀንሲውና በመንግሥት የልማት ድርጅት ገዢ መካከል የሚነሳ ክርክር የሚቀርበው ሥልጣን ላለው የፌደራል ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

3/ The residual assets and liabilities following the decision of the Ministry, in accordance with Article 6 (5) of this proclamation, on the transfer of assets and liabilities of public enterprise being converted into a share company, shall be transferred to the Trustee.

4/ The provision of Sub Article (1) and ( 2 ) of this Article shall similarly be applicable with respect to the transfer of rights and obligation of public Enterprises returned to their former owners by the decision of the Agency Pursuant to Proclamation No 110/1995.

5/ Employees' pension coverage existing before the privatization of any enterprise shall continue without interruption. The new owner of a Public Enterprise shall respect employers' obligations imposed by the appropriate laws with regard to employees' pension.

## 13. <u>Settlement of Disputes</u>

1/ Disputes arising between the Agency and a buyer of a Public Enterprise shall be referred to the appropriate Federal Court unless the parties have agreed in their contract to submit such disputes to a specific arbitration process or tribunal.

https://ethiodata.et/

፪/ ተዋዋይ ወገኖች ክርክራቸው በግልግል ዳኝነት አካል እንዲታይ የተስማሙ ከሆነ፣ የግልግል ሂደቱ በውሉና አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል ።

## ፲፬. ስለታክስ

፩/ ታክስ የሚያርፍባቸውን ገቢዎች መወሰንን በተመለከተ የንብረት የእርጅና ቅናሽ ስሌት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት በተደረገው የልማት ድርጅቶች ዋጋ ግምት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ሆኖም የጨረታው ዋጋ አነስተኛ ከሆነ ገዢው በከፈለው ትክክለኛ ገንዘብ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

፪/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተወሰነውን የንብረቶቹን ዋጋ ዝርዝር ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ ኤጀንሲው ከንብረት ባለቤትነት ሰነድ ጋር በተያያዘ የቀረጥ ቴምብር የተከፈለባቸውን ለገዢው የተላለፉ ንብረቶች ዋጋ ዝርዝርንም ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ Where the parties have agreed to submit their disputes to an arbitration tribunal, the proceedings thereof shall be conducted in accordance with the provisions of their contract and that of the Civil Procedure Code.

## 14. Taxation

1/ For the purpose of determining taxable income, the calculation of depreciation of assets shall be based on their valuation done in accordance with Article 7 of this Proclamation; provided, however, that it shall be based on the actual amount paid by the buyer where the tender price is lower.

2/ The Agency shall send to the concerned Tax Authority the breakdown of asset values determined in accordance with Sub-Article 1 of this Article.

3/ The Agency shall also send to the concerned Tax Authority the breakdown of values of assets transferred to the buyer and which are subject to the payment of stamp duty in relation to documents of title to property.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፭. ከፕራይቬታይዜሽን የተገኘ ገንዘብን ስለመጠቀም

ከፕራይቬታይዜሽን ከተገኘ ገንዘብ ላይ ለክንውኑ የተደረገው ወጪ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሚኒስቴሩ በሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ይደረጋል፡፡

### ፲፮. የመተባበር ግዴታ እና የኤጀንሲው ኃላፊነት

፩/ ማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙን በማስፈጸም ሂደት የሚጠየቀውን መረጃ ወይም ድጋፍ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለኤጀንሲው የሚተላለፉ መረጃዎችና ለገዢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡

፫/ ከባለቤትነት ማስረጃዎች፣ ከአገልግሎት ውሎች እና ከንግድ ፈቃዶች ዝውውር ጋር በተያያዘ ገዥው ፎርማሊቲዎችን ለማሟላት የሚያጠፋው ጊዜ የጊዜ ገደቡን ለማስላት ታሳቢ አይሆንም፡፡

### ፲፯. ሕገወጥ ባለይዞታዎችን ስለማስለቀቅ

፩/ ወደ ግል እንዲዛወር የተደረገ የልማት ድርጅት ሕንፃን ወይም ቅጥር ግቢን በሕገወጥ መንገድ በመያዝ ርክክብ እንዳይፈጸም ያወከ ሰውን ለማስለቀቅ የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የይዞታውን ሕጋዊነት የሚያሳይ መከላከያ

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 15. Use of Proceeds from Privatization

Any proceeds from privatizations shall be paid net of the costs of the transaction into an Industrial Development Fund Bank account administered by the Ministry.

### 16. Duty to Cooperate and the Responsibilities of the Authority

1/ Any Federal or Regional Government Organ or Official shall have the duty to cooperate in furnishing any information or rendering any assistance requested in the course of implementing privatization transaction.

2/ Without limiting the generality stated in Sub-Article (1) of this Article, the time limit for furnishing information to the Agency and providing required services to buyers shall be determined by the Agency.

3/ Time spent waiting for the buyer to comply with formalities in relation to the transfer of title deeds, utility contracts and licenses shall not be considered for the purpose of calculating the time limit.

### 17. Eviction of Illegal Occupants

1/ A court to which an application of suit is lodged for the eviction of a person alleged to illegally occupy the building or premises of a privatized Public Enterprise and impede the handover thereof, shall, unless a

https://ethiodata.et/

ካልቀረበለት በስተቀር በ፴ (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ የማስለቀቂያ ትእዛዝ በመስጠት ውሳኔውን ያስፈጽማል፡፡

statement of defense showing the legality of the occupation is submitted to it, issue and enforce an eviction order within thirty (30) days.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፹፯ መሠረት በኤጀንሲው ውሳኔ ለቀድሞ ባለቤቶቻቸው በሚመለሱ ንብረቶችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የይዞታውን ሕጋዊነት የሚመለከት መከላከያ ተቀባይነት አይኖረውም።

2/ The provisions of sub-Article (1) of this Article shall also be applicable with respect to the restitution of properties by the decision of the Agency pursuant to Proclamation No. 110/1995 provided, however, that any defense regarding the legality of the occupation shall not be entertained.

## ፲፰. የተሻሩ እና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች

፩/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፮/፲፱፻፺፩ (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 18. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Privatization of Public Enterprises Proclamation No. 146/1998 (as amended) is hereby repealed.

2/ No Law, Regulation, Directive or Practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

## ፲፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ከዚህ አዋጅ መውጣት በፊት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፮/፲፱፻፺፩ (እንደተሻሻለው) መሰረት ከፕራይቬታይዜሽን ጋር ተያይዞ ለተደረጉ ውሎችና ፍጻሜ ላላገኙ ጉዳዮች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 19. Transitional Provision

Any Existing contract related with privatization and issues which are not concluded under Privatization of public Enterprizes Proclamation No.146/1991 (Amneded) shall remain enforce in respect of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

## ፳. ተፈጻሚነት ያለው ሕግ

፩/ ነባር ድርጅትን ለማስፋፋትና ለማሻሻል ስለሚሰጡ ማበረታቻዎች እንዲሁም የውጭ ዜጎችና ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስክ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ ስለሚጠበቁላቸው መብቶች አግባብነት ባላቸው ኢንቨስትመንት ሕጎች የተደነገጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በተዛወረላቸው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ በኢንቨስትመንት ሕጉ ለሀገር ውስጥ ባለሀብት የተሰጠው ትርጉም ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም መንግሥትንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አይጨምርም፡፡

## ፳፩. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት

## 20. Applicable Laws

1/ Modification, Expansion of priorly existed enterprizes and also Foreign citizens and investors who are render on investment sectors obtain incentives and rights on the basis of appropriate investment laws shall to effect on those public Enterprises transfered into privatization .

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the definition given to “domestic investor “ under the investment Proclamations does not include Government or public enterprise for the purpose of implementation of this Proclamation.

## 21. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa On the 10th Day of July 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESDIENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://ethiodata.et/